# ተራጋሚ ንጉስ

ህዝቡ በጠየቀ ፣ በደሉ ሲከፋ
ምን ፣ አመስጋኝ አለ ፣ እያሉ ውረፋ
ንጉስ ፣ ምን ነካቸው ፣ ማስተዋሉ ጠፋ?
    መድረክ እንዳየናት ፣ የፓስተር ጠለፋ
    በሃሰት ድራማ ፣ እንደ ፣ ኢዩ ጩፋ
    በጩበጣ እመኑኝ ፣ ይሉናል በይፋ
    ብስጭት ያበዛል ፣ የቆረጠ ተስፋ
ጠረጠሩኝ ብሎ ፣ ከመድፈቅ አረፋ
ለምን መልስ ፣ አይሰጥም ፣ ከህዝብ ከሚጋፋ ።

አሜን ፣ አሜን በሉ ፣ የሚል ፓስተር ፣ ነግሶ
የፈራነው ሆነ ፣ መጣ ተመልሶ
    ቅዝምዝም ወደዚያ ፣ ፍየል ፣ ወዲህ ማዶ
    ሃዘን ይቀመጣል ፣ እራሱ አሳርዶ
መች ያንቀላፋና ፣ የኦነጉ እረኛ
ወደ ስሜን ፣ ሲሄድ ፣ ሆነ እንጂ ፣ ዳተኛ
    ያሳምነው ፅጌ ፣ የዶክተር አምባቸው
    ይሄው ፣ ሞተው ቀሩ ፣ ተኝቶ አምላካቸው
ኢትዮጵያ ፣ አምላክ የላት ፣ ቢኖርም ዳተኛ
የነአብይ አምላክ ፣ ነው ፣ ንቁና የማይተኛ
    እንዲህ ነው ፣ እንግዲህ ፣ ንጉስ ሲተብቱ
    ፀሃይ ላይ ፣ ተሰጣ ፣ ወጥቶ ማንነቱ
ፓስተሩ እያወሩ ፣ በመጋዘን ልሳን
መች ተደመጠና ፣ የኛ ጩኸት ፣ ድርሳን
መግባባቱ ጠፍቶ ፣ ጭራሽ ተረሳሳን ።

እሹሩሩ የሚወድ ፣ ሁሌ ፣ እንደ ሙሽራ
መሞገስ ካልሆነ ፣ ትችት የሚፈራ
ተንኮሉ ሲጋለጥ ፣ የሚያስነሳ አቧራ
ዶላር አልታለብ ፣ ባለች ፣ ላሜ ቦራ
        ሊበሏት ያሰቧት ፣ ቁራ ፣ ብትሆን ጅግራ
        ምሷ ፣ እርግማን ሆነ ፣ ምስኪን ዲያስፖራ ።

የተኩላ ቆራቢ ፣ ደርሶ ፣ ቅዱስ መሳይ
የበግ ለምድ ለባሽ ፣ ሃሳዊና አስመሳይ
መስከረም አይጠባ ፣ ሁሌም ፣ ጉድ ሳይታይ
የትላንቱን ድጋፍ ፣ ዞሮ እንኳን ፣ የማያይ
ሟርተኛ መጣብን ፣ ዛሬስ ባደባባይ
    ተራጋሚ ንጉስ ፣ ተነስቷል ፣ ቃል አባይ
    መች ይሆን ፣ ኢትዮጵያ ፣ ይቅር የምትባይ ።

ታዛቢው

July 2, 2019